QUICKNOTES mcps

February 12, 2019 QuickNotes

**የ 2018-2019 የትምህርት ዓመት እስከ ጁን 14 ተራዝሟል**

በቅርቡ የተከሰተው ከባድ የአየር ሁኔታ MCPS ለሦስት ቀናት ት/ቤቶችን ለመዝጋት አስገድዶታል። በ 2018-2019 የ MCPS ትምህርት ካላንደር የሚያካትተው 182 የትምህርት ቀናት፣ በሜሪላንድ ስቴት ቢያንስ ከሚጠበቀው ገደብ በሁለት ቀናት የበለጠ ነው። በነዚህ ቀናት ት/ቤቶች በመዘጋታቸው ምክንያት፣MCPS ከተመደቡት የማካካሻ ቀናት አንዱን ቀን በስቴት-መስፈርት የተመደበውን የትምህርት ቀናት ለማሟላት መጠቀም ይኖርበታል። የትምህርት ዓመቱ አሁን እስከ ጁን 14/2019 ይራዘማል። የመጨረሻው የትምህርት ቀን ለሁሉም ተማሪዎች ቀድመው የሚለቀቁበት ቀን ይሆናል። በአስቸኳይ የአየር ሁኔታ ምክንያት በተጨማሪ ት/ቤት ከተዘጋ ሌላ ተጨማሪ የማካካሻ-ቀናትን የመጠቀም አስፈላጊነት ያስከትላል። በድንገተኛ/አስቸኳይ የአየር ሁኔታዎች ምክንያት አራተኛ ቀን መዝጋት ካለብን፣ ቀጣዩ አስቸኳይ የአየር ሁኔታ ማካካሻ ቀን ረቡእ፣ ጁን 5/2019 ይሆናል። MCPS መጥፎ የአየር ሁኔታዎችን በአንክሮ እየተከታተለ በትምህርት ቤት ካላንደር ላይ ተጽእኖ የሚያስከትል ወቅታዊውን መረጃ ማሳወቅ/ማስተላለፍ ይቀጥላል። ስለ MCPS የትምህርት ቤት ካላንደር የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ይህንን ድረገጽ ይመልከቱ፡- http://www.montgomeryschoolsmd.org።

**የሪፖርት ካርዶች ፌብሩዋሪ 6 ተሰራጭቷል።**

ለወላጆች፡- የእርስዎ ልጅ ሪፖርት ካርድ ፌብሩዋሪ 6 ወደ ቤት ተልኳል። ሪፖርት ካርዶች በሚቀጥሉት ቀናትም ወደ ቤት ይላካሉ፡-

- ኤፕረል 16
- ጁን 24

በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጆች ያሏቸው ወላጆች የልጆቻቸውን ውጤቶች ዓመቱን በሙሉ በ *myMCPS* parent portal ላይ መከታተል ይችላሉ። የ1ኛ ደረጃ ተማሪ ያላቸው ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ሪፖርት ካርድ ውጤት እና ትምህርት የተከታተሉበትን ሁኔታ ለማየት ይችላሉ።

**ለኤሌሜንታሪ የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች ማመልከቻዎችን ኣሁን ማግኘት ይቻላል**

በ MCPS ለኤሌሜንታሪ ት/ቤት የቋንቋዎች ኢመርሽን/ትምህርት ፕሮግራሞች/language immersion ማመልከቻዎች አሁን ይገኛሉ። ለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ማመልከቻ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ዓርብ ኤፕሪል 26/2019 ነው።

የኤሌሜንታሪ ት/ቤት የቋንቋዎች ኢመርሽን/ትምህርት ፕሮግራሞች/language immersion የሚጀምሩት በሙዓለ ህፃናት ሆኖ የሚቀርቡትም በቻይኒዝ፣ፈረንሳይኛ እና በስፓኒሽ ነው። ዲስትሪክቱ ሶስት ስፓኒሽ፣ ሁለት ፈረንሳይኛ

እና ሁለት ቻይኒዝ የኤሌሜንታሪ ቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች በካውንቲው ውስጥ በሰባት ቦታዎች ያቀርባል። ሁለቱ የፈረንሳይኛ ፕሮግራሞችና ከስፓኒሽ ፕሮግራሞች አንዱ ጠቅላላ ኢመርሽን ናቸው። በጠቅላላ ኢመርሽን፣ ሁሉም መሰረታዊ የትምህርት አይነቶች፣ የንባብ/የቋንቋ ኪነ ጥበባትን ጨምሮ፣ ትምህርት የሚቀርብባቸው በጥናት/በትኩረት ቋንቋ ነው። ከስፓኒሽ ፕሮግራሞች ሁለቱና ሁለቱ የቻይኒዝ ፕሮግራሞች ከፊል ኢመርሽን ናቸው። በከፊል ኢመርሽን፣ የተወሰኑ መሰረታዊ የትምህርት አይነቶች በትኩረቱ ቋንቋ ይቀርባሉ። ስለ ኤሌሜንታሪ ኢመርሽን ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ እና የ Immersion Interest Form/ኢመርሽን ፍላጎት ፎርም ለማውረድ፣ የልዩ ፕሮግራሞች ድረ-ገጽ ይጎብኙ። እንዲሁም ፎርሞቹ በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ይገኛሉ።

ልዩ ዓይነት አገልግሎት/እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችም ለዕጣ/ሎተሪ ማመልከት ይችላሉ። በእጣ/ሎተሪ ሂደት የሚሳተፉ ተማሪዎች በሙሉ ሜይ አጋማሽ ላይ ውጤቱ ይገለጽላቸዋል። ለፕሮግራሙ ያልተመረጡት ተማሪዎች በተጠባባቂ ዝርዝር ይመዘገባሉ። ተማሪዎች በተጠባባቂ ዝርዝር/ሊስት ላይ የሚመዘገቡት በዘፈቀደ ቅደም ተከተል ሲሆን ወደ ፕሮግራሙ የሚጋበዙት ቦታ በተገኘ ጊዜ ነው።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወላጆች Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS) በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2540 መደወል ይችላሉ።

[የኤሌሜንታሪ ኢመርሽን ፕሮግራሞች]

[የኤለመንተሪ ኢመርዥን ፕሮግራም ፈላጊዎች የስብሰባ ቀኖች]

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሰመር እድሎች አውደርዕይ/MCPS Summer Opportunities Fair**

ማርች 7 በሚደረገው አውደ ርእይ በትምህርት ቤት እድሜ ክልል ላይ ለሚገኙ ልጆቻቸው ወላጆች በርካታ የሰመር እድሎችን ለመቃኘት ይችላሉ። ስለ ሰመር ካምፖች፣ ፕሮግራሞች እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች ለማስረዳት የአካባቢ እና የሪጅናል አገልግሎት ሰጭዎች ይገኛሉ። ወላጆች የፕሮግራም ሠራተኞችን ሊያገኟቸው፣ማመልከቻዎችን ለመውሰድ፣እና ስለ ፋይናንስ ድጋፍ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ይችላሉ። ፕሮግራሙ ከ7 እስከ 8:30 p.m. በ Carver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive, Rockville ይካሄዳል። ስለ ፕሮግራሙ በሚከተለዉ ድረ-ገጽ ይመዝገቡ፡- http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/ ወይም 240-314-4825 ይደዉሉ።

**በተጨማሪ**

**በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሰመር ካምፕ ምዝገባ እየተካሄደ ነው**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምርጥ የሰመር ካምፕ ፕሮግራሞችን በካውንቲው ውስጥ አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይሰጣል። በርካታ ካምፖች በፍጥነት የሚሞሉ ስለሆነ ወላጆች ስለ ሰመር ወራት በቅድሚያ እንዲያቅዱ እናደፋፍራለን።

ስለ ሰመር ካምፖች መመሪያ በድረ-ገጽ ላይ ለማየት Montgomery County Recreation ድረ-ገጽ ይጎብኙ። የሰመር ካምፕ መመሪያ የህትመት ቅጂዎች በመዋኛ ስፍራዎች እና በማህበረሰብ የመዝናኛ ማዕከሎች ይገኛሉ።

ከጃኑዋሪ 22 ጀምሮ የሰመር ካምፕ ምዝገባ እየተካሄደ ነው። በተጨማሪ ወላጆች በዚህ ድረ-ገጽ ለሰመር ካምፕ መመዝገብ ይችላሉ www.ActiveMONTGOMERY.org።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ/Montgomery County Recreation በስልክ ቁጥር፡- 240-777-6840 ይደውሉ።

**ለዓመቱ የካውንስለር ሽልማቶች ጥቆማ ማቅረብ እየተካሄደ ነው**

ተማሪዎችን በመደገፍ፣ከሥራ ባልደረቦች እና ከተማሪ ቤተሰቦች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመንከባከብ እና በማዳበር፣ እና የላቀ የመሪነት ሚና በመጫወት ልቀው የሚታዩ የትምህርት ቤት ካውንስለር ያውቃሉ? ለ MCPS የት/ቤት አማካሪ የዓመቱ ሽልማቶች ተወዳዳሪዎችን መጠቆሚያ ጊዜው አሁን ነው። እነዚህ ሽልማቶች የአማካሪዎችን ለዓላማ መቆምና ከባድ ስራን—በኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛ፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በያንዳንዳቸው ደረጃዎች—ያከብራሉ። ሠራተኞች፣ ከአስተዳዳሪዎች፣ ከወላጆች እና ከተማሪዎች ጥቆማዎችን ማቅረብ ይችላሉ።

ለመሰየም፣ አማካሪዎች በ MCPS በተግባር በአማካሪነት የሚሰሩ መሆን ያለባቸውና ለስርአቱ ቢያንስ ለሶስት አመት የሰሩ መሆን አለባቸው። ተሰያሚዎች የላቀ አመራር በተጨማሪ ማሳየት አለባቸው፤የተማሪዎችን ግላዊ ፍላጎቶች የሚገነዘቡ፣ተሰጥኦአቸውን የሚያበረታቱና በራስ መተማመናቸውን የሚኮተኩቱ፤ ከጓዶች፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦቻቸውና ከማህበረሰቡ ጋር የትብብሮሽ ግንኙነቶች ማዳበር፤ እና ውሳኔ አወሳሰድን ለማራመድ በአሀዞች መጠቀም።

የመጠቆሚያ ፎርሞች እዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

ጥቆማ **ዓርብ፣ ፌብሩዋሪ 15 ይጠናቀቃል።** ማመልከቻ የሚቀርብበት የሠዓት ገደብ **ዓርብ፣ ማርች 29 በ** 4 p.m. ነው። የጥቆማ ማቴሪያሎችን በ Google Docs ለ Jennifer Hitchcock, School Counseling Services, Office of Student and Family Support and Engagement በኤሌክትሮኒክስ ይላኩ።

ለጥያቄ የስልክ ቁጥር፦ 240-740-5641 ይደውሉ።

[የኣመቱ የኮንሰልታንት ሽልማት ፕሮግራም]

[የት/ቤት ምክር እገልግሎቶች]

**ለወላጆች የልዩ ትምህርት አውደጥናት ፌብሩዋሪ 20 ይካሄዳል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ረቡዕ፣ ፌብሩዋሪ 20 ለወላጆች እና ለሞግዚቶች የልዩ ትምህርት አውደጥናት ያካሄዳል። በክዉነቱ ወቅት፣ ስለ...
ወላጆች በቡድን የተከፋፈሉ ክፍለ ጊዜያትን መከታተል ይችላሉ

- የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር አገልግሎቶች/Secondary Transition Services
- በተለዋጭ/አማራጭ የትምህርት ውጤቶች ላይ ተማሪዎችን መደገፍ
- ጭንቀት-ስጋት ያለበ(ባ)ት ተማሪን የመደገፍ ስትራተጂ
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሠላም ስትራቴጂዎች
- ሁለንተናዊ የማስተማር ፕላን ንድፍ
- ለልዩ ትምህርት ብቁ መሆን

አውደጥናቱ የሚካሄደው በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Richard Montgomery High School ከ 7–8:30 p.m. ይሆናል። ጥያቄ የሚቀርብ ከሆነ የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል። [በድረ-ገጽ] ይመዝገቡ።

**Kojo Nnamdi በትምህርት ቤቶች ስለ ብዝሃነት እና የስኬታማነት ክፍተት ላይ የሚካሄድ ውይይት ያቀናብራል**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ስለ ብዝሃነት እና የስኬታማነት ክፍተትን በሚመለከት በ WAMU 88.5 Kojo Nnamdi (ኮጆ ናምዲ) የተቀናበረ ታወንሆል ዉይይት ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 26 ይካሄዳል።

ፕሮግራሙ የሚካሄደው ከ 6–8 p.m. በ Silver Spring Civic Building, 1 Veterans Place, Silver Spring ይሆናል። በር የሚከፈተው በ 6 p.m. ሲሆን 6:30 p.m. ሪኮርድ ማድረግ ይጀምራል። የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ጃክ ስሚዝ/Superintendent Jack Smith፣ ከመድረክ ውይይት አቅራቢዎች አንዱ ሲሆኑ፣ስለ MCPS ትምህርት ቤቶች ጭንቅንቅ፣ የተማሪዎች ስኬት ክፍተት እና የትምህርት ቤት ክልል የመሣሣሉትን ርእሶች እንደሚዳስሱ ይጠበቃል።

ይህ ፕሮግራም በተከታታይ ከሚደረጉት የኮጆ ናምዲ ዝግጅት አካል ነው/The Kojo Nnamdi Show's 20ኛ ዓመት በዓል። ስለ ዝግጅቱ የበለጠ መረጃ [እዚህ] ይገኛል።

ዝግጅቱ ለማህበረሰብ በነፃ ክፍት ይሆናል፣ ነገር ግን አስቀድሞ መመዝገብ እንደሚያስፈልግ በጥብቅ ይመከራል። በቅድሚያ ሳይመዘገቡ ለሚገቡ ሰዎች የመቀመጫ ዋስትና ላይኖር ይችላል። [እዚህ] ይመዝገቡ። ሁነቱ በሚካሄድበት ወቅት የህፃናት እንክብካቤ/ጥበቃ ይኖራል።